

# ምንቀረሽ ኢትዮጵያ

አካልሽ፡ ተቆረሠ፣
ወርድ ቁመትሽ አነሠ፣
በውስጥሽ እራብ እርዛት ነገሠ።
እንዳትገቢ ወጥተሽ፣
እንዳይዘረጋ እጅ እግርሽ፣
ዙሪያውን በር ዘጉብሽ።
ልጆችሽ ከምር ተገፍተው ቢሰደዱ፣
አልቀናቸውም መንገዱ፣
በእየሄዱበት ተዋረዱ።
መጠጊያ አጡና መድረሻ፣
ማጠብ ቢሄዱ ያረብ ቅርሻ፣
ከፎቅ ተወረወሩ እንደመናምንቴ ቆሻሻ።
አድባራትና ገዳማትሽ ተደፈሩ፣
መስጅዶችሽ ተወረሩ፣
ልጆችሽ በማንነታቸው አፈሩ።
የጀግኖችሽ መታሰቢያዎች ፈረሱ፣
ኒሻን መዳሊያዎችሽ ተወረሱ፣
ታሪካዊ እሴትችሽ ለተተኪው እነዳይደረሱ።
ምንቀረሽ እንግዴህ ሃገሬ፣
የሚተላለፍ ለነገ ከዛሬ፣
ለነበር እንኳ ለወሬ።
ቆመን እያየን ሁሉም ጠፋ፣
ጭላንጭል ሳይተው ለተሰፋ፣
አለ የሚባል የታሪክ አንጋፋ።
ልጆችሽ አብረው እንዳይውሉ፣
ያገኙትን ተካፍለው እንዳይበሉ፣
በዘር በሀይማኖት ተከፋፈሉ።
እየው ቆመዋል ለእየ ብቻቸው፣
አንድነት ጠፍቷል በመካከላቸው፣
ኢትዮጵያ እስኪቢሰሙሽ ተማጸኛቸው።

እናታለም ይብቃ ዝምታ በይ እንጅ እሪ፣
ድምጽሽን ከፍ አድርገሽ ተጣሪ፣
ሰውስ ጠፍቷልና ምናልባት ቢሰማሽ ፈጣሪ፣
ሰውስ ጠፍቷልና ምናልባት ቢሰማሽ ፈጣሪ።

ከማተቤ መለሰ ተሰማ